ራስን መግዛት

አራት የዶርም ጓደኞማቾች የተለያየ ፀባይን ተላብሰው በአንዲቷ ዶርማቸው ይኖራሉ። ፈቃዱ ለትምህርቱ ትልቅ ትኩረት ከመስጠቱ የተነሣ ዘወትር በጥናት ይጠመዳል። ብርሃኑ ኪስ በመጫወትና በማየት ከክፍልና ከጥናት ውጪ ያለውን ጊዜውን ያሳልፋል። አንተነህ ደግሞ ቀልድ የሚያበዛና ፊልምን ማየት የሚያዘወትር ነው። አስማማው የቤተ-ክርስቲያን አገልጋይ ሲሆን ለትምህርቱም ጊዜውን በአግባቡ ያውላል።

ትእይንት 1

(ከንጋቱ 12 ሰዓት)

ፈቃዱ፡- /አስማማው ከዶርም ሲወጣ ተመለከተና ፈቃዱ ከአልጋው ብድግ ብሎ ተነሥቶ ጥናቱን ጀመረ። እጆቹን እያወራጨና እያሰላሰ ያጠናል። በመሀል ይቆምና ያጠናውን እየተናገረ በዶርሙ ይዘዋወራል።/ . . . ‹‹Formoterol and Salmoterol for nocturnal asthma . . . ኧ ኸ . . . epinephrine should not be given at nerve endings. . .

/የፈቃዱ ድምፅ የቀሰቀሰው ብርሃኑ ይነቃና/

- ብርሃኑ፡- ፍቁ ዛሬ ቀኑ ምንድንነው?
- አንተነህ፡- /በአልጋው ላይ እንደመንጎራደድ ይልና/ እንዴት ይጠፋሻል! ሐሙስ የቀን ቅዱስ፤ ይልሻል። ነይ እስቲ ብሬ መቀደሱን እንጀምረው አንድ ጌም እንጫወት።
- ፈቃዱ፡- ፈተና ደርሷል፤ ማጥናት ይሻለሀል። ፋርማ አይቸክልም ጊዜ ይፈልጋል።
- አንተነህ፡- /የፈቃዱን ንግግር ተቀብሎ/ ደሞ ቢቸክልም ነገዉ ይጠፋል።
- ብርሃኑ፡- ከሰዓት የምቸክለው ፋርማ ነው፤ ባይሆን ፍቁ ምንድንነው ምታነቢው?
- ፈቃዱ፡- ጉድ ማን ተመችቶኛል፤ ስላይዱም አሪፍ ነው።
- አንተነህ፡- ስላይዱን መቀለም ነው ባክሽ፤ ሌላው እኮ አስተማሪዎቹም አያርፉትም።
- ብርሃኑ፡- አንቺ ደሞ ስላይዱ እንዲገባሽ መጽሐፍ ታነቢያለሽ እንጂ በዚህ አጭር ጊዜ አስተማሪዎቹን ለመብለጥ መሰለሽ።
- አንተነህ፡- ኤውልሽ ብሬ ሜዲሲን ውስጥ የሚያስፈልግሽ ውጤት እንጂ ዕውቀት አይደለም። ስላይድ ደሞ ፈተናውን ለመሥራት በቂ ነው።
- ፈቃዱ፡- አንቱ ተፎግረሻል ነገ እኮ የምታክሚው በዕውቀትሽ ነው እንጂ በውጤት አይደለም።
- አንተነህ፡- ያኬማ ክሊኒካል ሲገባ ነው ነገሩ ፊጥ ሚደረገው የአሁን ዕውቀት ምንም አይጠቅምም።
- ፈቃዱ፡- አይ አንቱ አንቺ ገና አልነቃሽም፤ መሸቶብሻል፤ የእውነት መሸቶብሻል፤ ዛሬ የቋጠሩት ለነገ ይሆናል ሲባል አልሰማሽም።

- ብርሃኑ፡- አይ ፍቁ ይህ አባባልሽ እኮ ነው ብርቱ ያደረገሽ፡፡ /ብርሃኑ ይህን ብሎ የፈቃዱን እጅ በአድናቆት ሲመታ አስማማው ወደ ዶርም ይገባል፡፡/
- አስማማው፡- እንዴት አደራችሁ?
- ፈቃዱ፡- እግዚአብሔር ይመስገን
- አንተነህ፡- አስሜ አድረናል እንደ ጉድ፤ እየተወንን በሙድ፤
- አስማማው፡- ምን ማለት ፈልገሽ ነው?
- አንተነህ፡- ኧረ አሁን አይነገርም፤ ከፈተና በኋላ ወይ ደግሞ ጥናት ሲደብረን እነግርሻለሁ፡፡
- አስማማው፡- ካልክ ይሁን፤ ፈተና ግን መቼ ተወሰነ?
- ፈቃዱ፡- Next week አርብ
- ብርሃኑ፡- በ ለ ው. . . አንድ ሳምንት ይጨመራል ተብሎ አልነበር እንዴ?
- ፈቃዱ፡- ዲኑ አይሆንም አለ፤
- አንተነህ፡- ጉድ መጣ አለች ያሸብር እናት... ካፊ የሚሄድ የለም?
- ብርሃኑ፡- እንሂድ ነይ...

/ብርሃኑና አንተነህ ይወጣሉ፡፡ አስማማው ኮምፒዉተሩን እየከፈተ.../

- ፈቃዱ፡- ክላስ እስክንገባ ትንሽ እናድማ፤ ምን ይመስልሻል፤

- አስማማው፡- የኔም ዕቅድ እሱ ነው፡፡

/አስማማውና ፈቃዱ ጥናታቸውን ቀጠሉ፡፡ ... በመሀል ይጠያየቃሉ አንዱ አንዱን ያስረዳል፤... ከጥቂት ቆይታ በኋላ ብርሃኑና አንተነህ ከሌላ ዶርም ጓደኛቸው ከእንዳሻው ጋር ስለኪስ እያወሩ ወደ ዶርም ይመጣሉ፡፡/

- ብርሃኑ፡- ሩኒ የመታት ኪስ!... ሩኒ የመታት ኪስ!... በሕይወቴ እንዲህ ያለ ጎል አይቼ አላውቅም! /በአንክሮ ይናገራል/
- እንዳሻው፡- በጣም ይገርማል! በረኛው ብቻ አይደለም አርሰን ቬንገር ከነ ተጫዋቾቹ ፈዘዘ እኮ! በስመ አብ... /ይህን እያወሩ ወደ ዶርም ይገባሉ፤/
- አንተንህ፡- አሁን ስንት ሰዓት ነው? /እያለ የፈቃዱን ላፕቶፕ ጎንበስ ብሎ ተመለከተና/ ለክላስ 20 ደቂቃ ብቻ ነው የሚቀረን ብሬ እስከዛ አንድ ጌም...
- ብርሃኑ፡- የማታው ሽንፈት አልበቃህም? /ብሎ ከአንተነህ ጋር በኮምፒዉተር ጌም ሊጫወቱ ጎን ለጎን ይቀመጣሉ/
- እንዳሻው፡- ዳኛ ነኝ /ብሎ ከጎናቸው ይቀመጣል/
  /3 ሰዓት ሲሞላ ሁሉም ክፍል ለመግባት ሲወጣ አንተነህ ‹‹ላጥና ባክህ፤ ብዙ ይቀረኛል/ ብሎ ጠረጴዛ ላይ ለማጥናት ይቀመጣል/
  /ከዶርም እየወጡና እየሄዱ ሳለ/
- አስማማው፡- በነገራችን ላይ ዛሬ 12 ሰዓት ላይ ጉባኤ እንዳለ አልረሳችሁም አይደል?
- ብርሃኑ፡- 11 ሰዓት ኪስ እጫወታለሁ፤ ከዚያ እስከ 12 ብጨርስም ስለሚደክመኝ የምመጣ አይመስለኝም፡

- ፈቃዱ፡- አ ዛሬ መከለስ አለብኝ አስሜ አይመቸኝም፡፡
- አስማማው፡- ባትቀሩ ጥሩ ነው...

ትእይንት 2

(ከሳምንት በኋላ ከፈተና መልስ)

/ አስማማው ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ከቀናት በፊት የጀመራትን መንፈሳዊ መጽሐፉን ያነባል፡፡ ብርሃኑ ለስፖርት የምትሆነውን ልብስ እየለበሰ ነው፤ አንተነህ ደግሞ አልጋው ላይ ተዘርሯል፡፡ ፈቃዱ በሩን በርግዶ ይገባና/

- ፈቃዱ፡- ወይኔ ተመታሁ!
- አንተነህ፡- /ከአልጋው እንደመነሳት እያለ/ ማን መታሽ ፍቂ? /ጓደኞቹ ሲስቁ ተመልክቶ/ ወይኔ ፈቃዱ ፍቂ፤ ተመታሁ እላለሁ ባለመነቅነቂ፤
- ፈቃዱ፡- /እንደ መበሳጨት ይልና/ አንተ ደሞ ሁሌ ትቀልዳለህ፡፡ አጥንቼ እንዳላጠናሁ፤ ጨፍጭፈዋለሁ ስል ጨፍጭፎ ለቀቀኝ...ኡህ.../ እያለ በኃይል ሲተነፍስ/
- አስማማው፡- ፍቂ ተረጋጋ አንዳንዴ ይገጥማል፤ ፈተናው ደግሞ ለሁሉም ከባድ ስለነበር ሃሳብ አይግባህ፡፡
- ፈቃዱ፡- እንዳንተ እኮ የሚያረጋጋ ነው የጠፋው፡፡ አስሜ ግን እንዴት ነው ይህ መረጋጋት ካንተ ተርፎ ለሰው የሚሆነው?!!! ካንተ በላይ ነው ያጠናሁት፤ነገር ግን ያንተን ያህል መደሰትና መረጋጋት አልቻልሁም፡፡
- አስማማው፡- በራሴ የተረጋጋሁና ደስተኛ አይደለሁም ፍቂ፤ ቤተ-ክርስቲያን የምትለግሰኝ የዘወትር ምግብና መጠጤ ይህ ነው፡፡ ቤተ-ክርስቲያን የምሄደው ጊዜዬን ለማጥፋት ወይ ደግም ለመዝናናት አይደለም፤ በርግጥ ቤተ-ክርስቲያን ሲኬድ አእምሮ ነፃ ይሆናል፤ ከከተማ ወጥተህ ብትዝናና እንኳን የማታገኘው ነፃነት ይከበሀል፡፡ ከዚህ ባሻገር ቤተ-ክርስቲያን እንደጠራ መስታዎት ማንነትህን አጉልታ ታሳየሀለች፤ የምታስተምርህ ለመንገድህ ብርሃን ለሰውነትህ ፀዳል ነው፤ ለሕይወትህም ታላቅ ስንቅ ትቋጥርልሀለች፡፡ እስቲ ከዚህ መጽሐፍ አሁን ያነበከትን የአቡነ ሺኖዳ ምክር ላንተም ላንብብልህ፡፡... (‹‹የሕይወት መዐዛ›› ገጽ 49 የመጨረሻው አንቀጽ ያነብለታል)

/እያነበበ ሳለ ብርሃኑ መውጣቱን ትቶ አንተነህም ከአልጋው ተነሥቶ አስማማውን መስማት ጀመሩ/

- ብርሃኑ፡- መንፈሳዊ ሕይወት ባንተ ዘንድ ዋጋውን አጥቷል፡፡ /ብርሃኑ እንደመተከዝ ብሎ ቃላቱን እየረገጠ አንገቱን እየነቀነቀ ይናገራል፡፡/
- ፈቃዱ፡- የምትፈልገውን ሁሉ አግኝተህ ነፍስህ ብትጎዳ ለአንተ ምንድን ነው ጥቅሙ? /አቀርቅሮ ይህንኑ ይደግማል/
- /አንተነህ አቀርቅሮ መሬቱን እያየ ይቆያል/
- አስማማው፡- አሁን ቁም ነገር የጨበጣችሁ ይመስለኛል ጓዶች፡፡ ቤተ-ክርስቲያን ጥሩ ንጹሕ መስታዎት ናት ማንነትህን ታሳየሀለች ማለቴ ለዚህ ነው፡፡ ሰው ማለት የሥጋና የነፍስ ጥምር ነው፡፡ ጠዋት ተነሥተን ካፌ፣ ለምሳም ካፌ፣ ለራትም ካፌ ተመላልሰን

ለሥጋ የሚሆነን ምግብ መጠጥ እንደምንፈልገው፤ ለነፍሳችንም ምግብና መጠጥ መስጠት አለብን፡፡ ነፍስ እንደ ሥጋ ባትገዝፍም፤ ትራባለች ደግሞም ትጠማለች፡፡ ራቧና ጥሟን ለማስታገሥ ደግሞ ቤተ-ክርስቲያን ሄደን ምግብና መጠጥ ልንሸምትላት ይገባል፡፡ ጉባኤ እንከታተል ቤተ-ክርስቲያን እንሂድ የምላችሁ ለዚህ ነው፡፡ ያልተረዳነው ነገር ካለ ቀስ ብለን እናውቀዋለን፤ ለኛ ተብሎ የሚደረገው ዝግጅት ደግሞ እኛ አቴንሽን አንሰጠውም እንጂ እኛን የሚያስደስት ነው፡፡

- አንተነህ፡- ዛሬ ጉባኤ አለ አስሜ?
- አስማማው፡- አዎ፤ Post exam ብዙ ሰው ይመጣል ተብሎ ተዘጋጅቷል፡፡
- አንተነህ፡- ኧረ Post exam የለ Before exam ከዛሬ ጀምር ጉባኤ on time ኸች ነው፡፡
- ፈቃዱ፡- አስሜ በጣም ነው የማመሰግነው፡፡ የሕይወቴን መሠረት የነገርከኝ መሰለኝ፡፡ እንኳን ጉባኤን መታደም አይደለም አብሬህ ማገልገል እፈልጋለሁ፡፡
- አስማማው፡- ደስተኛ ነኝ፤ ለኔም ትልቅ እድል ነው፡፡ /ሞቅ ያለ ሰላምታ ይሰጣጣሉ፡፡/ /...እንዳሻው የስፖርት ልብሱን ለብሶ ወደ ዶርም በመግባት/
- እንዳሻው፡- ብሬ አረፈድን እኮ እስካሁን አንተን ስጠብቅህ ነበር፣ ቀረህ፤
- ብርሃኑ፡- እንዴ እኔ ዛሬ አልጫወትም ጉባኤ መሄድ አለብኝ፡፡
- እንዳሻው፡- ትንሽ ተጫውተህ እኮ ትደርሳለህ፡፡
- ብርሃኑ፡- አይ ከደከመኝ በደንብ መማር አልችልም፡፡ ተረጋግቼ ብማር ይሻለኛል፡፡
- እንዳሻው፡- በይ እሺ ቸው፡፡ /ብሎ ከዶርም ይወጣል፡፡/
- አንተነህ፡- አስሜ ያንን ሕልም እኮ ከነገርኩህ በኋላ ሌላ ተመሣሣይ ሕልም አየሁ፡፡
- አስማማው፡- አንቱ አንድ ነገር ላስታውስህ፡፡ እዚህ ግቢ የመጣኸው ተምረህ ራስህንና ቤተሰቦችህን እንዲሁም ርዳታህን የሚፈልጉ ሰዎችን ለመርዳት ነው፡፡ ፊልምና ጌሞች መዝናኛ እንጂ ቋሚ ሥራዎች ሊሆኑህ አይገቡም፡፡ በሕልምህ ተዋናይ ሆነህ የምትሠራባቸው ሆረሮች (Horrors) የዚህ ውጤት ናቸው፡፡ ስለዚህ አንቱ ለፊልምና ለጌም የሰጠኸው ጊዜ ከፍለህ ለቤተ-ክርስቲያን አድርገው፡፡ ሌሊት የሚያስደነግጡህንም ነገሮች ከአንተ ይርቃሉ፡፡
- አንተነህ፡- Thank you አስሜ!
- አስማማው፡- /የስልኩን እስክሪን አየና/ የጉባኤ ሰዓት ደርሷል በቃ እንሂድ . . . /እንዳለ ሁሉም ማስታወሻውን ይዞ ከዶርም ይወጣል፡፡/

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር

ንብተ ጊዮርጊስ

መጋቢት፣ 2007 ዓ.ም